# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## የአርብ ፕሮግራም

1. **በአርብ ፕሮግራም** እግዚአብሔር ግሩም የጸሎት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎት እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

2. በተለያየ ምክኒያት ወደኋላ የተመለሱ ወገኖችን ለመፈለግና ለመጎብኘት ሽማግሌዎች እቅድ አውጥተው እየተንቀሳቀሱ ስልሆን የምናውቀውና መጎብኘት አለበት የምትሉትን ስም ለወንድም ጌቱ እንድትሰጡ እናሳስባለን።

3. በቤተክርስቲያናችን በለዪ ልዩ አገልግሎት ውስጥ ያላችሁ አገልጋዮች በሙሉ ቀጥሎ በተገለጹት ቀናት ከእሁድ አምልኮ ፕሮግራም በኋላ ከሽማግሌዎች ጋር ስብሰባ ስለሚኖረን በጊዜ ሰሌዳችሁ መሰረት እንድትገኙ በጌታ ፍቅር እናሳስባለን።

⇒ ጁላይ15/2018 ኮሚኒኬሽን ሚዲያ

⇒ ጁላይ22/218 የእህቶች አገልግሎት

⇒ ጁን29/2018 ርህራዬ አገልግሎት

"ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
⇒ Yeec.org App ጭነዋል?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

---

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።"
(ዮሐ. 10፡10)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**July 15, 2018** | **ሐምሌ 8፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

ጸሎት መሪ................. ወንድም ሰለሞን ወመኔ

አምልኮ....................... የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

ፕሮግራም መሪ .......... ወንድም አያሌው አስፋው

ቃል ............. ወንድም ረድኤቱ ካሳ

ማጠቃለያ ................. ፕሮግራም መሪ

### የሳምንቱ ጥቅስ

"በእርሱ ሕይወት ነበረች፥
ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች።
ብርሃንም በጨለማ ይበራል፥
ጨለማም አላሸነፈውም።"
(ዮሐ. 1፡4-5)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመኔ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ግርማ ካሳ

### የሕይወት ተስፋ!

*"በክርስቶስ ኢየሱስ እንደሚሆን የሕይወት ተስፋ፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ፥ ለተወደደው ልጁ ለጢሞቴዎስ፤ ከእግዚአብሔር አብ ከጌታችንም ከክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋና ምሕረት ሰላምም ይሁን።" (2 ጢሞ. 1፡1-2)*

ከላይ በሰፈረው ሰላምታ ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ አንድ መሰረታዊ የክርስትናን አስተምህሮ ሲጠቅስ እንመለከታለን። የኸውም "በክርስቶስ ኢየሱስ እንደሚሆን የሕይወት ተስፋ" በሚለው ሃረግ ውስጥ እንደተቀመጠው የሕይወት ተስፋ ያለው በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ የሚገልጸው ክፍል ነው። ሐዋሪያው በመንፈስ ልጁ ለሆነው ለጢሞቲዎስ በጻፈው በዚህ ሁለተኛ ደብዳቤ ለየት ባለ መልኩ ሰላምታውን ስለ ህይወት ተስፋ በመግለጽ ይጀምራል። የምድር ሕይወቱና አገልግሎቱ በክርቶስ ኢየሱስ ባለ የሕይወት ተስፋ ላይ የቆመ እንደሆነ ያጸናል። ያለበትንም ሁኔታ የሚመለከተው ከዚህ የሕይወት ተስፋ አንጻር ነው።

ለመሆኑ ህይንን ደብደቤ ሲጽፍ ሐዋሪያው በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ነበር። ይህንን ደብዳቤ በጻፈበት ወቅት ሐዋሪያው በኔሮ አስተዳደር በሮም ታስሮ የነበረበት ወቅት ነው። ስለዚህም በቁጥር 8 ላይ ልጁን ጢሞቲዎስን "በእስረኛው በእኔ አትፈር" ይለዋል። እንደዚሁም ወንጌልን በመስበኩ እንደ ክፉ አድፋጊ እንደታሰረ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል እንደማይታሰር ይናገራል። (1ጢሞ. 2፡9) ብዙዎችም ከርሱ ፈቀቅ እንዳሉና በብቸኝነት ያለበት ጊዜም እንደሆነ ክፍሉ ይጠቅሳል። ("በእስያ ያሉቱ ሁሉ ከእኔ ፈቀቅ እንዳሉ ታውቃለህ" (2ጢሞ. 1፡15))። ዴማስ ይኅንን አለም ወዶ ትቶታል፤ ሌሎችም ትተውት ወደ ተለያየ ስፍራ ሄደዋል፤ አንጥረኛው እስክንድሮስ እጅግ ከፍቶበታል፤ እንዲሁም በፊተኛው ሙግቱ ማንም አልደረሰለትም -- ሁሉም ትተውታል። (2ጢሞ. 4፡ 9-17) በዚህ ሁሉ ግን ሐዋሪያው በምሬትና በትስፋ መቁረጥ ውስጥ ሳይሆን ያለው ይልቁንም የኖረለትን፣ የቀመሰውንና የሚመጣውን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን የሕይወት ተስፋ እያሰበ ከመከራው በላይ ሆኖ መከበሩን ይጠባበቃል።

በተለይም ደግሞ ሐዋሪያው ይህንን ክፍል ሲጽፍ በምድር ያለው አገልግሎቱ እየተጠናቀቀ እንደሆነ አውቋል። ("በመሥዋዕት እንደሚደረግ፥ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና፥ የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአል።" (2ጢሞ. 4፡6) ነገር ግን የሚጽፈው ስለሞት ሳይሆን ስለ ሕይወት ነው። የሚጽፈው ስለ ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን ስለ ተስፋ ነው። እንዲያውም የተጠበቀለትን አክሊል እያሰበ ደስ ይለዋል። በብዙም ያመሰግናል። ማንም አጠገቡ ባይኖርም ጌታ ግን ከርሱ ጋር እንዳለና የጌታ ሃሳብ በርሱ እንደሚፈጸም ያውቃል። ("ዳሩ ግን የስብከቱ ሥራ በእኔ እንዲፈጸም አሕዛብም ሁሉ እንዲሰሙት፥ ጌታ በእኔ አጠገብ ቆሞ አበረታኝ፥ ከአንበሳ አፍም ዳንሁ። ጌታም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል ለሰማያዊውም መንግሥት ይጠብቀኛል፤ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።" 2ጢሞ. 4፡ 17-18)) የጳውሎስ ትኩረት በመከራው ላይ ሳይሆን በተገለጠውና ሊገለጥ ባለው በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነው የሕይወት ተስፋ ላይ ነበር። መከራውንም ያስረሳው ሕይወቱ በዚህ የሕይወት ተስፋ ብረሃን በመሞላቱ ነበር። መጽሐፍ እንደሚለን ጌታችን የመጣው ሕይወት እንዲሆንልንና እንዲበዛልን ነው። (ዮሐ. 10፡10) ጨለማውን ሊያሸንፍ የሚችል ሕይወት ያለው በእርሱ ብቻ ነው። (ዮሐ. 1፡5) በኛ ውስጥ የክርስቶስ ሕይወት ስላለ ጨለማ ሊውጠን አይችልም። የሐዋሪያው ትምክህት በክርስቶስ ባለ የሕይወት ተስፋ ነበር። የኛስ?